# ለነፃ እና ቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦች እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

ለነፃ ወይም ቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦች ማመልከቻ ለመሙላት እንዲረዳዎት እባክዎ እነዚህን መመሪያዎች ይጠቀሙ፡፡ ምንም እንኳን ልጅዎ በ WISH CHARTER ዉስጥ ከአንድ ትምህርት ቤት ዉስጥ በላይ ቢሳተፉም፤ በአንድ ቤተሰብ ዉስጥ ማስረከብ የሚጠበቅብዎት እንድ ማመልከቻ ብቻ ነዉ፡፡ ልጅዎ ለነፃ ወይም ቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦች ማለፉን ለማረጋገጥ፤ ማመልከቻዉ ሙሉ በሙሉ ተሞልቶ መጠናቀቅ አለበት፡፡ እባክዎ እነዚህን ትዕዛዞች በደንብ ይከተሉ፡፡ የመመሪያዎቹ እያንዳንዱ ደረጃ ከማመልከቻዎ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ በየትኛዉም ጊዜ ቀጥሎ ምን እንደሚያደርጉ እርግጠኛ ካልሆኑ፤ እባክዎ Kimberlie Traceski at WISH Charter – kimberlie@wishcharter.org – 310 410 9940 ያግኙ፡፡

**ማመልከቻዉን ሲሞሉ እባክዎ እስክሪብቶ ይጠቀሙ (እርሳስ አይጠቀሙ) በተጨማሪም በንፅህና ለመፃፍ የቻሉትን ጥረት ያድርጉ፡፡j**

## ደረጃ 1: ሕፃናት፣ ልጆች እና እስከ 12 ክፍል ድረስ ያሉትን ሁሉንም የቤተሰብ አባላት ይዘርዝሩ

ስንት ሕፃናት፣ ልጆች እና ተማሪዎች በቤትዎ ዉስጥ እንደሚኖሩ ይገሩን፡፡ የቤተሰብዎ አባል ሆነዉ ለመቆጠር የግዴታ ዘመድዎ መሆን የለባቸዉም፡፡

**መዘርዘር ያለብኝ ማንን ነዉ?** ይህንን ክፍል ሲሞሉ፤ እባክዎ ከዚህ በታች ያሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሁሉንም የቤተሰብዎን አባላት ያካትቱ:

- 18 ዓመት ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች እና በቤተሰቡ ገቢ የሚተዳደሩ;
- ቤት የለሽ፣ ስደተኛ ወይም የጠፉ ወጣት ልጅ የሚለዉን የሚያሟሉ ወይም በማደጎ አስተዳደግ ዉስጥ ከእርስዎ እንክብካቤ በታች ያሉ;
- እድሜ ሳይለይ በ [WISH Charter ትምህርት የሚከታሉ ተማሪዎች፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| **A) የእያንዳንዱን ልጅ ስም ይዘርዝሩ፡፡** የእያዳንዱን ልጅ ስም ይፃፉ፡፡ ለእያዳንዱ ልጅ የማልከቻዉን አንድ መስመር ይጠቀሙ፡፡ ስሞችን ሲፅፉ፤ በእያንዳንዱ ሳጥን አንድ ፊደል ይፃፉ፡፡ የመፃፊያ ቦታ ካልበቃዎት፤ ያቁሙ፡፡ በማመልከቻዉ ላይ ከተዘጋጀዉ ቦታ የሚበልጥ ቁጥር ልጆች ካልዎት፤ የተጨመሩትን ልጆች ሁሉንም አስፈላጊ መረጃ ያካተተ ሁለተኛ ተጨማሪ ወረቀት ያያይዙ፡፡ | **B) ይህ ልጅ በ [WISH Charter የሚማር ተማሪ ነዉ?** የትኞቹ ልጆች በ[WISH Charter እንደተማሩ ለማሳወቅ፤ “ተማሪ” ከሚለዉ ረድፍ ስር ‘አዎ’ ወይም ‘አይደለም’ የሚለዉን ይምረጡ፡፡ ‘አዎ’ የሚለዉን ከመረጡ፤ በስተቀኝ ባለዉ ‘ክፍል’ በሚለዉ ረድፍ ላይ ተማሪዉን የክፍል ደረጃ ይፃፉ፡፡ | **C) የማደጎ ልጆች አልዎት?** ከተዘረዘሩት ዉስጥ የማደጎ ልጆች ካሉ፤ ከልጁ ስም ጎን “የማደጎ ልጅ” የሚለዉን ሳጥን ይምረጡ፡፡ ማመልከቻዎ ለማደጎ ልጅ ብቻ ከሆነ፤ **ደረጃ 1** ን እንደጨረሱ ወደ **ደረጃ 4** ይሂዱ፡፡ <u>ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ የማደጎ ልጆች እንደ ቤተሰብዎ አባል ስለሚቆጠሩ በማልከቻዎ ላይ መዘርዘር አለባቸዉ፡፡</u> ለማደጎ እና የማደጎ ላልሆኑ ልጆች ካመለከቱ፤ ወደ ደረጃ 3 ይሂዱ፡፡ | **D) ቤት የለሽ፣ስደተኛ ወይም የጠፉ ልጆች አሉ?** በዚህ ክፍል ከተዘረዘሩ ልጆች የትኛዉም ይህንን መስፈርት እንደሚያሟላ ካመኑ፤ ከልጁ ስም አጠገብ “ቤት የለሽ፣ ስደተኛ፣ የጠፉ” የሚለዉን ሳጥን ምልክት ያድርጉ እና <u>የማልከቻዉን ሁሉንም ደረጃዎች ያሟሉ፡፡</u> |

## ደረጃ 2: የትኞቹም የቤተሰብ አባላት በአሁኑ ጊዜ በ SNAP፣ TANF፣ ወይም FDPIR ይሳተፋሉ ?

**የትኛዉም የቤተሰብ አባል(እርስዎንም ጨምሮ) ከታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ባሉ የእርዳታ ፕሮግራሞች በአሁኑ ጊዜ ተሳታፊ ከሆኑ፤ ልጅዎ ለነፃ የትምህርት ቤት ምግቦች ብቁ ናቸዉ:**

- የተጨማሪ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP) ወይም TELEPHONE - (916) 651-8848 / EMAIL - piar@dss.ca.gov
- ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF) ወይም TELEPHONE - (916) 651-8848 / EMAIL - piar@dss.ca.gov
- በሕንድ ጎተራ የምግብ ክፍፍል ፕሮግራም (FDPIR)

| | |
|---|---|
| **A) የትኛዉም የቤተሰብዎ አባል ከላይ በተዘረዘሩት ፕሮግራሞች የማይሳተፉ ከሆኑ:**<br>• **ደረጃ 2** ን ባዶዉን ትተዉ ወደ **ደረጃ 3** ይሂዱ፡፡ | **B) የትኛዉም የቤተሰብዎ አባል ከላይ በተዘረዘሩት በየትኛዉም ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ከሆኑ:**<br>• ለ SNAP፣ TANF፣ ወይ FDPIR የመዝገብ ቁጥር ይፃፉ፡፡ የሚጠበቅብዎ እንድ የመዝብ ቁጥር ማቅረብ ብቻ ነዉ፡፡ ከእነዚህ ፕሮግራሞች በአንዱ ከተሳተፉ እና የመዝገብ ቁጥርዎን ካላወቁ፤ https://yourbenefits.laclrs.org/ybn/Index.html / (866) 613 3777 ያግኙ፡፡<br>• ወደ **ደረጃ 4** ይሂዱ፡፡ |

## ደረጃ 3: ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ገቢዎን ይዘግቡ

**ገቢዬን እንዴት ልዘግብ ?**

- ቤተሰብዎ የሚዘግበዉ ገቢ እንዳለዉ ለመወሰን፤ ከማመልከቻዉ በስተጀርባ **“<u>የአዋቂዎች የገቢ ምንጮች</u>”** እና **“<u>የልጆች የገቢ ምንጮች</u>”** በሚል ርዕስ የተፃፈዉን ሠንጠረዥ ይጠቀሙ፡፡
- ሁሉንም መጠኖች በጥቅል ገቢ ብቻ ይዘግቡ፡፡ ሁሉንም ገቢዎች በዶላር ይዘግቡ፡፡ ሳንቲሞችን አያካትቱ፡፡
  - ጥቅል ገቢ ከግብር በፊት ያለዉ ጠቅላላ ገቢ ነዉ
  - ብዙ ሰዎች ገቢ ብለዉ የሚያስቡት “ወደ ቤት የሚወሰድ” መጠን እንጂ “ጥቅል” መጠንን አይደለም፡፡ በዚህ ማመልከቻ ላይ የሚዘግቡት ገቢ ግብር፣ የዋስትና ክፍያ፣ ወይም ሌላ ምንም አይት መጠን ለመክፈል አለመቀነሱን ያረጋግጡ፡፡

## ደረጃ 3: ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ገቢዎን ይዘግቡ

- ምንም አይነትየሚዘገብ ገቢ ከሌለ በየትኛዉም ስፍራ “0” ይፃፉ፡፡ ባዶ ወይም ክፍት የተተወ የትኛዉም የገቢ ስፍራ እንደ ዜሮ ይቆጠራል፡፡ If you write ‘0’ ከፃፉ፤ ወይም የትኛዉንም ስፍራ ቦዶ ከተዉ፤ ምንም ዓይነት ገቢ እንደሌልዎት እያረጋገጡ (እየማሉ) ነዉ፡፡ የገቢ ሰራኞች የቤተሰብዎ ገቢ በስህተት እንደተዘገበ ከጠረጠሩ፤ የልጅዎ ማመልከቻ ይመረመራል፡፡
- ከእያዳንዱ ስፍራ በስተቀኝ ያለዉን ሳጥን በመምረጥ በምን ያህል ጊዜ እያዳንዱን የገቢ አይነት እንደሚቀበሉ ምልክት ያድርጉ፡፡

### 3.A. በልጆች የሚገኘዉን ገቢ ይዘግቡ

**A) *በልጆች ያኙትን ወይም የተቀበሉትን ሁሉንም ገቢዎች ይዘግቡ፡፡*** በቤትዎ ዉስጥ ላሉ በደረጃ 1 ለተጠቀሱት ሁሉም ልጆች “ጠቅላላ የልጅ ገቢ” በሚለዉ ሳጥን ዉስጥ የጥምር ጥቅል ገቢዉን ይዘግቡ፡፡ ለማደጆ ልጆች ከቀሪዉ ቤተሰብዎ ጋር ካመለከቱ፤ የማደጎ ልጆችን ገቢ ብቻ ይቁጠሩ፡፡

***የልጅ ገቢ ምንድን ነዉ?*** የልጅ ገቢ ማለት ከቤተሰብዎ ዉጭ የተቀበሉት፤ ለልጆችዎ በቀጥታ የተከፈለ ገንዘብ ነዉ፡፡ ብዙ ቤተሰቦች የልጅ ገቢ የላቸዉም፡፡

### 3.B በአዋቂዎች የሚገኘዉን ገቢ ይዘግቡ

**እዚህ መዘርዘር ያለብኝ ማንን ነዉ?**

- ይህንን ክፍል ሲሞሉ፤ እባክዎ <u>ምንም እንኳ ባይዛመዱም ወይም የራሳቸዉ ገቢ ባይኖራቸዉም</u>፤ ከእርስዎ ጋር የሚኖሩትን ሁሉንም አዋቂ የቤተሰብዎን አባላት እና ከእርስዎ ጋር ገቢና ወጪን የሚጋሩትን ያካትቱ፡፡
- ***እነዚህን አያካትቱ:***
  - ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ነገር ግን በቤተሰብዎ ገቢ ድጋፍ የማያገኙ እና ለቤተሰብዎ ገቢ መዋጮ የማያደርጉ፡፡
  - ቀደም ብሎ **በደረጃ 1** የተጠቀሱ ልጆች እና ተማሪዎች፡፡

| | | |
|---|---|---|
| **a) አዋቂ የቤተሰብ አባላት ስሞች ይዘርዝሩ፡፡** “አዋቂ የቤተሰብ አባላት ስሞች (የመጀመርያ እና የመጨረሻ)”በሚሉት ሳጥኖች ዉስጥ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ስም ይፃፉ፡፡ <u>**በደረጃ 1** የተዘረዘሩ የማንኛዉንም ቤተሰብ አባላት አይዘርዝሩ፡፡</u> **በደረጃ 1** የተዘረዘረ ልጅ ገቢ ካለዉ፤ **በደረጃ 3, ክፍል A** ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ፡፡ | **b) ከስራ የተገኘን ገቢ መዘገብ፡፡** ሁሉንም ከስራ የተገኘን ገቢ በማልከቻዉ ላይ “ከስራ ተገኙ ገቢዎች” በሚለዉ ክልል ዉስጥ ይዘግቡ፡፡ ይህ በአብዛኛዉ በመስሪያ ቤቶች በመስራት የሚገኝ ገንዘብ ነዉ፡፡ የግል-ቅጥረኛ የንግድ ባለቤት ወይም የእርሻ ባለቤት ከሆኑ፤ የተጣራ ገቢዎን ይዘግቡ፡፡<br><br>***በግሌ-ቅጥርተኛ ከሆንኩስ?*** ከስራዉ የሚገኘዉን መጠን፤ እንደተጣራ መጠን ይዘግቡ፡፡ ይህ የተሰላዉ የጠቅላላ የንግዶዎ የስራ የእቅስቃሴ ከጥቅል ቅበላዎ ወይም ገቢዎ ላይ ተቀንሶ ነዉ፡፡ | **c) ከሕዝባዊ እርዳታ /የልጆች ዕገዛ/አበል የሚገኝን ገቢ ይዘግቡ፡፡** በማልከቻዉ ላይ “ሕዝባዊ እርዳታ/ የልጅ ዕገዛ፣ አበል” ዉስጥ የሚካተቱትን ሁሉንም ገቢዎች ይዘግቡ፡፡ <u>በሠንጠረዡ ላይ ያልተዘረዘረ የትኛዉም የሕዝባዊ እርዳታ ጥቅማ ይቅሞች ጥሬ ገንዘብ አይዘግቡ፡፡</u> ከ ልጅ ዕገዛ ወይም አበል ገቢ ከተቀበሉ፤ ፍርድ-ቤተ ያዘዘዉን ትዕዛዞች ክፍያ ብቻ ይዘግቡ፡፡ መደበኛ ያልሆነ ነገር ግን ቋሚ ክፍያዎች “ሌላ” ተብለዉ ለሚቀጥለዉ ክፍል መዘገብ አለባቸዉ፡፡ |
| **d) ከጡረታዎች/ የጡረታ ክፍያ/ ከሌሎች ከሁሉም የሚያገኙትን ገቢዎችን ይዘግቡ፡፡** በማልከቻዉ ላይ “ጡረታ/የጡረታ ክፍያ/ ሁሉም ሌሎች ገቢዎች” ቦታዎች የሚሆኑትን ሁሉንም ገቢዎች ይዘግቡ፡፡ | **e) ጠቅላላ የቤተሰብ መጠን ይዘግቡ፡፡** ጠቅላላዉን የቤተሰብ አባላት ቁጥር በተሰጠዉ “ጠቅላላ የቤተሰብ አባት (ልጆች እና አዋቂዎች)” ስፍራ ያስገቡ፡፡ ይህ ቁጥር **በደረጃ 1** እና **በደረጃ 3** ከተጠቀሰዉ የቤተሰብ አባላት ቁጥር ጋር እኩል መሆን አለበት፡፡ በማልከቻዉ ላይ ያልዘረዘሩ ምንም አይነት የቤተሰብ አባል ካልዎት፤ ወደ ኋላ ተመልሰዉ ይጨምሯቸዉ፡፡ የቤተሰብዎ መጠን ፤ለነፃ እና ቅናሽ ዋጋ ምግቦች ያላቸዉን ብቁነት ተፅዕኖ ስለሚያደርግ ሁሉንም የቤተሰብ አባላት መዘርዘር በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡ | **f) የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን የመጨረሻ አራት ቁጥሮች ያቅርቡ፡፡** አዋቂ የቤተሰብ አባል በተዘጋጀዉ ስፍራ ላይ፤ የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥራቸዉን የመጨረሻ አራት ቁጥሮች ማስገባት አለባቸዉ፡፡ የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር ባይኖርትም እንኳ ለጥቅማ ጥቅሞች ለማመልከት ብቁ ነዎት፡፡ ምንም አዋቂ የቤተሰብ አባላት የማሕራዊ ዋስት ቁጥር ከሌላቸዉ፤ ይህንን ስፍራ ባዶዉን ይተዉ እና በስተቀኝ “የማሕራዊ ዋስትና ቁጥር ከሌለ አይሆንም የሚለዉን ይረጡ SS#” የሚለዉን ሳጥን ምልክት ያድርጉ፡፡ |

## ደረጃ 4: የሚገኙበት መረጃ እና የአዋቂ ፊርማ

***ሁሉም ማመልከቻዎች በአዋቂ የቤተሰብ አባል መፈረም አለባቸዉ፡፡ ይህንን ማመልከቻ በመፈረም፤ የቤተሰቡ አባል የተዘገቡት መረጃዎች በሙሉ እዉነተኛ እና በተሟላ ሁኔታ መዘገባቸዉን አረጋግጧል፡፡ ይህንን ክፍል ከማጠናቀቅዎ በፊት፤ እባክዎ ከማመልከቻዉ በስተጀርባ ያለዉን የሚስጥራዊ እና የዜጎች መብቶች መረጃ ማንበብዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡***

| | | | |
|---|---|---|---|
| **A) የሚገኙበትን መረጃ ያቅርቡ፡፡** ይህ መረጃዎ የሚገኝ ከሆነ፤ አሁን የሚገኙበትን አድራሻ በተዘጋጀዉ ስፍራ ላይ ይፃፉ፡፡ ቋሚ አድራሻ ከሌልዎት፤ የልጅዎን ለነፃ ወይ ቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤቶች ብቁነት አያቀረዉም፡፡ስልክ ቁጥርዎን፣ የኢሜል አድራሻዎን፣ ወይ ሁለቱንም ማጋራት የእርስዎ ምርጫ ቢሆንም፤ ነገር ግን እርስዎን ማግኘት ከፈለገን በአፋጣኝ እንድናገኝዎት ይረዳናል፡፡ | **B) ስምዎን ይፃፉ እና ይፈርሙ፡፡** ማመልከቻዉን የሚፈርመዉን አዋቂ ሰዉ ስም እና ይህ ሰዉ “የአዋቂ ፊርማ” በሚለዉ ሳጥን ዉስጥ ይፈርም፡፡ | **C) የዛሬን ቀን ይፃፉ፡፡** በተዘጋጀዉ ስፍራ፤ በሳጥን ዉስጥ የዛሬን ቀን ይፃፉ፡፡ | **D) የልጆችን የዘር ወይም የጎሳ መለያዎችን ያጋሩ (አማራጭ)፡፡** ከማልከቻዉ በስተጀርባ፤ ስለ ልጆችዎ ዘር ወይም ጎሳ መረጃ እንዲያጋሩ እንጠይቅዎታለን፡፡ ይህ ስፍራ መሙላት አማራጭ ሲሆን፤ ልጆችዎ ለነፃ ወይም ቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦች ያላቸዉ ብቁነት ላይ ተፅዕኖ አይፈጥርም፡፡ |

## መመሪያዎች — የገቢ ምንጮች

| ለልጆች የገቢ ምንጮች | |
|---|---|
| **የልጅ ገቢ ምንጮች** | **ምሳሌ(ዎች)** |
| - ከስራ የሚገኝ ገቢ | - አንድ ልጅ የወር ደሞዝ ወይም ክፍያ የሚያስገኝ ቋሚ የሙሉ ወይም የከፊል ጊዜ ስራ አለዉ. |
| - ማሕበራዊ ዋስትና<br>- የአካል ጉዳተኝነት ክፍያዎች<br>- የማገገሚያ ጥቅማ ጥቅሞች | - አንድ ልጅ ዓይነ ስዉር ወይም አካል ጉዳተኛ ነዉ እናም የማሕራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች ይቀበላል<br>- አንድ ወላጅ አካል ጉዳተኛ፣ ጡረተኛ፣ ወይም ሞቷል እናም ልጁ የማሕበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች ይቀበላል |
| - ከቤተሰብ ዉጭ ከሆነ ሰዉ የሚገኝ ገቢ | - ጓደኛ ወይም የቅርብ ቤተሰብ አባል በቋሚነት ለልጅ የሻይ ገንዘብ ይሰጣል |
| - ከሌላ ከየትኛዉም ምንጭ የሆነ ገቢ | - አንድ ልጅ ከግል የጡረታ መዋጮ፣ አበል ወይም ባለአደራ ቋሚ ገቢ ይቀበላል |

| ለአዋቂዎች የገቢ ምንጮች | | |
|---|---|---|
| **ከስራ የሚገኙ ገቢዎች** | **የሕዝብ እርዳታ/ አበል/ የልጅ ዕገዛ** | **የጡረታ አበል/ ጡረታ/ ሌሎች ሁሉም ገቢዎች** |
| - ደሞዝ፣ ክፍያ፣ የገንዘብ ጉርሻዎች<br>- ከግል-ስራ የተጣራ ገቢ (እርሻ ወይም ንግድ)<br><br>በአሜሪካ ዉትድርና ዉስጥ ከሆኑ:<br><br>- መሰረታዊ ክፍያ እና የገንዘብ ጉርሻ (የጥል ክፍያ፤ FSSA ወይም የቤት ጭማሪ ክፍያ አያጠቃልልም )<br>- ለቤት ዉስጥ፣ ምግብ እና አልባሳት ጭማሪዎች | - የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች<br>- የሰራተኞች ካሳ<br>- ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (SSI)<br>- ከማዕከላዊ ወይም ከክልል መንግስት የገንዘብ ዕርዳታ<br>- የአበል ክፍያዎች<br>- የልጅ እገዛ ክፍያዎች<br>- ከዘመቻ ተመላሾች ጥቅማ ጥቅሞች<br>- ድንገተኛ ጥቅማ ጥቅሞች | - ማሕበራዊ ዋስትና (የባቡር ሃዲድ ዝርጋታ እና የጥቁር ሳምባ ጥቅማ ጥቅሞች)<br>- የግል ጡረታ ክፍያ ወይም ጉዳተኝነት<br>- ከባለአደራዎች ወይም ትረስት ያለ ገቢ<br>- አበሎች<br>- ኢንቨስት የማድረጊያ ገቢ<br>- የተገኘ ጥቅም<br>- የኪራይ ገቢ<br>- ከቤተሰብ ዉጪ በሆኑ ሰዎች የሚደረጉ ቋሚ የገንዘብ ክፍያዎች |

## አማራጭ — የልጆች የዘርና የብሔር ማንነት

ስለ ልጆችዎ ዘር እና ብሔር ጠይቀን መረጃ እንድናገኝ ተጠይቀናል፡፡ ይህ መረጃ በጣም ጠቃሚ እና ማህበረሰቡን በተሟላ ሁኔታ እንድናገለግል ይረዳናል፡፡ ለዚህ ክፍል ምላሽ መስጠት ግዴታ አይደለም እንዲሁም የልጆችዎን ነፃ ምግብ የማግኘት ወይም ቅናሽ ምግብ የማግኘት መብት የሚጎዳ አይደለም፡፡

**ብሔር (አንድ ይምረጡ)** ◯ ሂስፓኒክ ወይም ላቲኖ ◯ ሂስፓኒክ ወይም ላቲኖ ያልሆነ

**ዘር (አንድ ወይም ከዚያ በላይ ይምረጡ)** ☐ አሜሪካ ሕንዳዊ ወይም የአላስካ ተወላጅ ☐ እስያዊ ☐ ጥቁር ወይም አፍሪካ አሜሪካዊ ☐ የሐዋይ ተወላጅ ወይም የሌላ ፓስፊክ ደሴት ነዋሪ ☐ ነጭ

---

የ **ሪቻርድ ቢ. ረስል ብሔራዊ የትምሕርት ቤት የምሳ ህግ** የዚህን ማመልከቻ መረጃ ይፈልጋል፡፡ መረጃ መስጠት ግዴታ አይደለም፤ ካልሰጡ ግን ለልጅዎ ነፃ ወይም የቅናሽ ምግብ ልናፀድቅልዎት አንችልም፡፡ ማመልከቻው ላይ የፈረመው የቤተሰቡ አባል ያለውን የማሕበራዊ ዋስትና የመጨረሸዎቹን አራት ቁጥሮች ማካተት አለባችሁ፡፡ ማመልከቻው በማደጎ ልጅ ምትክ ሲሆን ወይም ለተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም(SNAP)፤ ለተቸገሩ ቤተሰቦች የሚሰጥ ጊዜያዊ እርዳታ ፕሮግራም(TANF) ወይም ለሕንዳዊያን የተያዘ የምግብ ክፍፍል ፕሮግራም(FDPIR) የመዝገብ ቁጥር ወይም ሌላ ለሕንዳዊያን የተያዘ የምግብ ክፍፍል ፕሮግራም ለልጅዎ ወይም ማመልከቻውን የፈረመው አዋቂ የቤተሰብ አባል የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር እንደሌለው ካሳወቁ የማሕበራዊ ዋስትና የመጨረሸዎቹ አራት ቁጥሮች አይጠየቁም፡፡ ልጅዎ ለነፃ ምግብ ወይም ለቅናሽ ምግብ ብቁ መሆኑን ለማወቅ እና ለምሳና ቁርስ አስተዳደርና አፈፃፀም ፕሮግራም ህጋዊ መረጃዎን ለመመዘን ፤ ለፕሮግራሞቻቸው የገንዘብ ወይም ጥቅማጥቅሞችን ለማወቅ እንዲረዳቸው የእርስዎን መረጃ እንጠቀማለን፡፡ ከትምህርት፤ ጤና እና አመጋገብ ፕሮግራሞች ፕሮግራሙን ለመከታተል ኦዲተሮች፤የፕሮግራሙ ህጎች መጣስ ለማየት እንዲረዳቸው የህግ አስፈፃሚ አካላት ጋር ልንጋራው እንችላለን፡፡

በፌደራል የዜጎች መብት እና ዩኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ አግሪካልቸር የዜጎች መብት አዋጅና ፖሊሲዎች፤ የዩኤስዲኤ ተወካዮች፤ ቢሮዎች ሰራተኞችና በዩኤስዲኤ ተሳታፊና አስተዳደር ማህበራት የዘር፤ የቀለም፤ ብሔር፤ ፆታ፤ የአካል ጉዳተኝነት፤ እድሜ፤ ወይም ከዜጎች መብት እንቅስቃሴ ፕሮግራም ወይም በዩኤስዲኤ የተዘጋጀ ወይም የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ማንኛውም እንቅስቃሴ መሠረት ያደረገ አድልዎ እንዳይደረግ ይከለክላል፡፡

በፌደራል የዜጎች መብት እና ዩኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ አግሪካልቸር የዜጎች መብት አዋጅና ፖሊሲዎች፤ የዩኤስዲኤ ተወካዮች፤ ቢሮዎች ሰራተኞችና በዩኤስዲኤ ተሳታፊና አስተዳደር ማህበራት የዘር፤ የቀለም፤ ብሔር፤ ፆታ፤ የአካል ጉዳተኝነት፤ እድሜ፤ ወይም ከዜጎች መብት እንቅስቃሴ ፕሮግራም ወይም በዩኤስዲኤ የተዘጋጀ ወይም የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ማንኛውም እንቅስቃሴ መሠረት ያደረገ አድልዎ እንዳይደረግ ይከለክላል፡፡

የፕሮግራሙን መረጃ ለመረዳት አማራጭ የመገናኛ መንገድ የሚያስፈልጋቸዉ አካል ጉዳተኛ ሰዎች (ለምሳሌ፡ ብሬል፣ትልቅ ዕትም፣ የድምፅ ቅጂ፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ፤ ወዘተ..) ለጥቅማ ጥቅም ያመለከቱበትን ወኪል (የከተማ ወይም የሀገር ዉስጥ) ማግኘት አለባቸዉ፡፡ መስማት የተሳናቸዉ፣ የሚቸግራቸዉ ወይም መናገር የሚያቅታቸዉ ሰዎች በጠቅላይ የመልዕክት አገልግሎት ዩኤስዲኤ ን በ (800) 877-8339 ማግኘት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የፕሮግራም መረጃዎች ከእንግሊዝኛ ዉጭ በሌሎች ቋንቋዎች ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

የመገለል ክስ መክፈት ከፈለጉ፤ በድሕረ ገፅ ላይ የሚገኘዉን የ ዩኤስዲኤ የፕሮግራም መገለል ክስ ፎርም በ፡ http://www.ascr.usda.gov/complaint_filing_cust.html እና በየትኛዉም የ ዩኤስዲኤ ቢሮ በመሙላት ወይም ለ ዩኤስዲኤ ደብዳቤ በመፃፍ እናም በደብዳቤዉ ዉስጥ በፎርሙ ላይ ያለዉን መረጃ በሙሉ ያቅርቡ፡፡ የክስ ፎርሙን ቅፅ ለመጠየቅ፤ በ (866) 632-9992 ይደዉሉ፡፡ የተሟላ ፎርም ወይም ለ ዩኤስዲኤ የሚላከዉን ደብዳቤ በዚህ አድራሻ ይስጡ፡

ሜይል፡ ዩ.ኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ አግሪካልቸር
የዜጎች መብት ረዳት ፀሐፊ ቢሮ
1400 የኢንዲፔንደንስ መንገድ, ኤስደብሊው
ዋሽንግተን, ዲ.ሲ. 20250-9410

ፋክስ፡ (202) 690-7442; ወይም

ኢሜል፡ program.intake@usda.gov.

ይህ ተቋም እኩል ዕድል የሚያቀርብ ነዉ፡፡

## እባክዎ አይምሉት — ለትምሕርት ቤት ጥቅም ብቻ

Annual Income Conversion: Weekly x 52, Every 2 Weeks x 26, Twice a Month x 24 Monthly x 12

Total Income: ______

How often? ◯ Weekly ◯ Bi-Weekly ◯ 2x Month ◯ Monthly

Household size: ______

**Categorical Eligibility** ☐

Eligibility: ◯ Free ◯ Reduced ◯ Denied

Determining Official's Signature ______ Date ______

Confirming Official's Signature ______ Date ______

Verifying Official's Signature ______ Date ______